መስከረም 6 ቀን 2013
አዲስ አበባ

# 89ኛ መደበኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት መስከረም 6 ባካሄደው 89ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. በቅድሚያ ምክር ቤቱ የተወያየው ኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ ለማቋቋም በቀረበ ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ ቀደም ሲል በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ስር የነበሩና በብረታብረት፣ በአውቶሞቲቭ፣ የእርሻ መሳሪያዎች ምርት፣ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ፣ የኮንስትራክሽን ማሽነሪና ፕላንት፣ እንዲሁም የፖሊመር ምርት ዘርፎች የተሰማሩትን ተቋማት በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ስር በማደራጀት የሃብት አጠቃቀሙን ውጤታማ ለማድረግ እና ወደ አትራፊነት እንዲሸጋገር ለማስቻል የማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ የተሰጡ ግብዓቶች ተካተው ረቂቅ ደንቡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመጨረሻም ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ እና በሩሲያ ፌደራሽን መካከል የኒውክሌ ሃይልን ለሰላማዊ ዓላማ ለመጠቀም የተደረገ የትብብር ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ ሁለቱ አገራት የ1968ቱ የኒውክለር መሣሪያዎች እሽቅድምድምን የሚከለክለውን አለምአቀፍ ስምምነት እና ከዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ጋር የገቡትን የስምምነት ባከበረ መልኩ የኒውክለር ኢነርጂን ለሠላማዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ማዋላቸው በአገራቱ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን በመግለጽ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የማጸደቂያ ረቂቅ አዋጁን አዘጋጅቶ አቅርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//